CITY OF CAMBRIDGE | Department of Transportation

የCentral Square ደህንነት ማሻሻያ ፕሮጀክት

Massachusetts Avenue፦ ከInman Street እስከ Lafayette Square

የመንገድ አቀማመጥ ለውጦች

የCambridge ከተማ አስተዳደር በCentral Square ውስጥ የተለዩ የብስክሌት መንገዶችን መጨመርን ያካተተ የደህንነት ማሻሻያ ሥራዎች እየሠራ ነው።
ምን እንደሚጠበቅ ከዚህ ይመልከቱ፦

የተለዩ የብስክሌት መንገዶች


የብስክሌት መንገዶች በእግረኛ መንገዶች ጥጎች ላይ የሚሠሩ ሲሆን፣ መንገዶቹም በብስክሌት የሚጓዙ ሰዎችን ከተሽከርካሪዎች የሚለዩ መከላከያዎች ይኖራቸዋል።

የትራፊክ ደህንነት ማሻሻያዎች

አዳዲስ የመንገድ ምልክቶች፣ የትራፊክ ምልክቶች እና ተጣጣፊ ምሰሶዎች (flex posts) ለሁሉም ሰው ይበልጥ አስተማማኝ እና ምቹ መንገድ ለመፍጠር ይረዳሉ።

የመኪና ማቆሚያ ቦታ ቅነሳ

ይህ ፕሮጀክት በመንገድ ዳር የሚገኙ የመኪና ማቆሚያ ቦታዎችን የሚቀንስ ይሆናል። በንድፉ ላይ አሁንም የማጠቃለያ ሥራዎች እየተሠሩ ቢሆንም፣ አሁን ካለው የመንገድ ዳር ቦታ ላይ ግን ወደ 75% የሚሆነውን ለዕቃ መጫን/ማውረድ እና ለመኪና ማቆሚያ እንደምናስቀር እንጠብቃለን።



ፕሮጀክቱ የሚሸፍነው ቦታ ካርታ

በቅርብ ቀን የሚካሄዱ የማኅበረሰብ ዝግጅቶች

ይምጡ ስለ ፕሮጀክቱም ይወቁ፣ አስተያየትዎንም ይስጡ። የመጀመሪያዎቹን ዕቅዶች የምናጋራ፣ በፕሮጀክቱ መርሃ-ግብር ዙሪያ፣ ስለሚያስገኛቸው ጥቅሞች እንዲሁም ስለሚያመጣቸው ለውጦች የምንወያይ ይሆናል።

እ.ኤ.አ ሐሙስ ኖቬምበር 12 ቀን 2026 ዓ.ም
የኦንላይን የመረጃ ክፍለ ጊዜ
ከ6:00 ፒ.ኤም እስከ 8:00 ፒ.ኤም
የZoom ዌብናር

እ.ኤ.አ ረቡዕ ዲሴምበር 2 ቀን 2026 ዓ.ም
ለሁሉም የማኅበረሰቡ አባላት ክፍት የሆነ በአካል የሚደረግ ስብሰባ
ከ5:30 ፒ.ኤም እስከ 7:30 ፒ.ኤም
Cambridge Senior Center
(የCambridge አረጋውያን ማዕከል)፣
806 Mass Ave

የMBTA ተወካዮች በCentral Square ጣቢያ የሚሠሩ አዳዲስ እና የተሻሻሉ ሊፍቶችን እንዲሁም ኤስካሌተሮችን ጨምሮ በታቀዱ የተደራሽነት ማሻሻያዎች ዙሪያ ውይይት ለማድረግ ለሁሉም የማኅበረሰቡ አባላት በአካል እንዲገኙ ክፍት በተደረገው ስብሰባ ላይ ይገኛሉ።

ለተጨማሪ መረጃ፣ የስብሰባ ዝርዝሮች ለማግኘት እና በኢሜይል ዝርዝሩ ላይ ለመመዝገብ ኪው.አር ኮዱን ስካን ያድርጉ

awolfe@cambridgema.gov
camb.ma/centralsqSIP

የንግድ ተቋማት፣ አስተያየቶቻችሁን መስማት እንፈልጋለን!

የሚከተሉትን ማወቅ እንፈልጋለን


- የመኪና ማቆሚያ እና የዕቃ መጫን/ማውረድ ፍላጎቶችዎ ምን ምን ናቸው?
- የትራንስፖርት ፍላጎቶችዎ ወይም የደህንነት ስጋቶችዎ ምን ምን ናቸው?

ያነጋግሩን

Andreas Wolfe
የመንገድ ንድፍ ፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅ
awolfe@cambridgema.gov
617 - 349 - 9162

የቀረበው የመንገድ ንድፍ፦ ከInman St እስከ Prospect St

የብስክሌት መንገዶች በእግረኛ መንገዶች ጥጎች ላይ የሚሠሩ ሲሆን፣ መንገዶቹም በብስክሌት የሚጓዙ ሰዎችን ከተሽከርካሪዎች የሚለዩ መከላከያዎች ይኖራቸዋል።



የቀረበው የመንገድ ንድፍ፦ ከPearl St እስከ Brookline St

የውጪ የመመገቢያ ቦታዎች እንዳሉ ይቀጥላሉ። የብስክሌት መንገዶች በእግረኛ መንገዶች ጥጎች ላይ የሚሠሩ ሲሆን፣ መንገዶቹም በብስክሌት የሚጓዙ ሰዎችን ከተሽከርካሪዎች የሚለዩ መከላከያዎች ይኖራቸዋል።

